© በኢትዮጵያብዝሀሕይወትኢንስቲትዩት
ግንቦት/2007

በUNEP/GEP የገንዘብ ድጋፍ በመድኃኒት ዕፅዋት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም፣ አርክቦት እና ጥቅምተጋሪነት አቅምግንባታ ፕሮጀክት የ ታተመ

**This Publication is financially supported by UNEP/GEF project Capacity Building for Access and Benefit Sharing and Conservation and Sustainable Use of Medicinal Plants in Ethiopia**

Printed by Wubishet Gutu p.p
+251-911-822834



# የጀነቲክ ሀብት አርክቦት እና ሀብቱን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ላይ ተመርኩዞ የወጣ የናጎያ ፕሮቶኮል ሰነድና አባሪ

በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ወደ አማርኛ የተተረጎመ

ግንቦት/2007
አዲስ አበባ

# የናጎያ ፕሮቶኮል

## የጀነቲክ ሀብት አርክቦት እና ሀብቱን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ላይ ተሞርኩዞ የወጣ ሰነድና አባሪ

**የብዝሀ ሕይወት ፅህፈት ቤት**

**ሞንትሪያል**

## የብዝህ ሕይወት ኮንቬንሽን

## የተባበሩት መንግስታት



በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ወደ አማርኛ የተተረጎመ

# የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት እንስቲትዩት

## ዋና ዳይሬክተር መልዕክት

ናጎያ ፕሮቶኮል እ.አ.አ በ1992 በብራዚል፣ሪዩዴጄኔሮ ከተማ የተፈረመ የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ሶስተኛ አላማን ተግባራዊነት የበለጠ ለማጠናከር በብዝሀ ሕይወት ስምምነት ላይ በመመርኮዝ የወጣ ዓለም አቀፍ የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ህግ ነዉ፡፡ የኮንቬንሽኑ አባላት ጉባኤ በ2004 እ.ኤ.አ በተካሄደው ሰባተኛ ስብሰባው የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪትን በተመለከተ የተቋቋመዉ ጊዜያዊ ኮሚቴ በዓለም አቀፍ ደረጃ ውይይትና ድርድር በማካሄድ ኮንቬንሽኑና የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 15 (የጀነቲክ ሀብት አርክቦት) እና አንቀፅ 8 (በ) (ባህላዊ እውቀት) እና የኮንቬንሽኑን ሶስቱንም አላማዎች በተሣካ ሁኔታ ለመተግበር እንዲቻል ስልጣን ሰጥቶታል፡፡ ከስድስት አመታት ድርድር በኋላ በጃፓን ሀገር በናጐያ ከተማ እ.ኤ.አ በጥቅምት 29ቀን/2010 በተደረገው የአባላት ጉባኤ አስረኛ ስብሰባ ላይ ፀድቋል፡፡ፕሮቶኮሉ በጀነቲክ ሀብት አርክቦትና ሀብቱን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞች ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ስምምነት ላይ በመመርኮዝ የናጐያ ፕሮቶኮል ሰነድ ተፈርሟል፡፡ ፕሮቶኮሉ ለጀነቲክ ሀብት አቅራቢዎች እና ተጠቃሚዎች የህግ ማዕቀፍ በማበጀትና ግልጽነትን በማስፈን

ጠንካራ መሠረት እንዲኖር በማድረግ ለኮንቬንሽኑ ሶስተኛው አላማ ተግባራዊነት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ፕሮቶኮሉን ተቀብሎ 2010 እ.አ.አ አፅድቋል፡፡

በትግበራ ሀደት የሚፈጠሩትን አሻም ጉዳዩችን ለመፍታት በፕሮቶኮሉ አንቀፅ 36 ሥር የተዘረዘሩ ቋንቋዎች ወሳኝ ቢሆኑም የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት እንስቲትዩት ፕሮቶኮሉ ለጀነቲክ ሀብት አርክቦት እና ባህላዊ እውቀት ጥበቃ እና ዘለቄታዊ አጠቃቀም ካለዉ ፈይዳ አንፃር የአገራችን ማህበረሰቦች በደንብ ተረድቶት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ፕሮቶኮሉን ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ እንድታተም አድርጎል፡፡

የአገራችን ሕዝቦች የነጎያ ፕሮቶኮል ለብዝሀ ሕይወት ሀብታችንና ባህላዊ ተያያዥ ዕዉቀት ጥበቃ፣በዘለቄታዊ አጠቃቀምና በተለይም የፍትሐዊና ተመጣጣኝ ጥቅም መጋራት ዓላማን ከማሳካት አንፃር ያለዉን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመረዳት ለህጉ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ መሆን ድርሻቸዉን እንዲወጡ እጠይቃለሁ፡፡

ዶ.ር ገመዶ ዳሌ

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት እንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ፅህፈት ቤት
የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካባቢ ፕሮግራም
413 ቅዱስ ጃኩዌስ ጎዳና ምእራብ፣ ሱት 800
ሞንትሪያል፣ ኩዩቤክ፣ ካናዳ፣ ኤች2ዋይ 1ኤን9
ፋክስ፡ +1(514) 2886588
ስልክ፡+1(514) 2882220
ኢሜይል፡ secretariat@cbd.int
ድረ ገጽ www.cbd.int

በብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ፅህፈት ቤት 2011
መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡የታተመው በ2011 እ.ኤ.አ
ካናዳ ታተመ ነው

የአለም አቀፍ ደረጃ መጽሐፍ ቁጥር (ISBN) 92-9225-306-9

ይህንን ህትመት ለትምህርታዊ ወይም ትርፍን መሠረት ላላደረገ ዓላማ ሲባል ያለ ልዩ የባለቅጂ መብት ፈቃድ ለመጠቀም የሚቻል ሆኖ ነገር ግን ምንጩ በአግባቡ መጠቀስ ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ሰነድ

ምንጭ ሆኖ የሚጠቀሰዉ የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ፅህፈት ቤት ነዉ፡፡

የውስጥ ካታሎግ ማኅደር የናጐያ ፕሮቶኮል የጀነቲክ ሀብት አርክቦት እና ሀብቱን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞችን ተመጣጣኝና ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ላይ በመመርኮዝ የወጣ ሰነድና አባሪ/ የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ፅህፈት ቤት፡፡

ማጠቃለያ፡ "ይህ መጽሔት የናጐያ ፕሮቶኮል የጀነቲክ ሀብት አርክብትና ሀብቱን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ላይ በመመሥረት የወጣ ሰነድና አባሪን የያዘ ነው"፡፡ በአታሚው የቀረበ

አለም አቀፍ ደረጃ የመጽሐፍ ቁጥር (ISBN) 92-9225-306-9

1. የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ሕግና አዋጅ
2. የጀነቲክ ሀብት ጥበቃ ሕግና አዋጅ
3. ብዝሀ ሕይወት ዓለምአቀፋዊ ትብብር
4. የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ
   i. የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን (1992 እኤአ)፣ ፕሮቶኮሎች፣ ወዘተ፣ 2010 ጥቅምት 29 (እ.ኤ.አ)
   ii. የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን አባላት ጉባኤ (ናጐያ፣ ጃፓን፣ 2010 እ.ኤ.አ)

iii. የተባበሩት መንግስታት

ኬ3488-ኤ48 2011

የናጕያ ፕሮቶኮል የጀነቲክ ሀብት አርክቦት እናሀብቱን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞችን ተመጣጣኝና ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ላይ በመመርኮዝ የወጣ ሰነድና አባሪ/ የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ፅህፈት ቤት፡፡

ማጠቃለያ፡ "ይህ መጽሔት የናጕያ ፕሮቶኮል የጀነቲክ ሀብት አርክብትና ከአጠቃቀማቸው የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊ ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ላይ በመመሥረት የወጣ ሰነድና አባሪን የያዘ ነው"፡፡ በአታሚው የቀረበ አለም አቀፍ ደረጃ የመጽሐፍ ቁጥር (ISBN) 92-9225-306-9

5. የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ሕግና አዋጅ
6. የጀነቲክ ሀብት ጥበቃ-ሕግ
7. ብዝሀ ሕይወት የዓለም አቀፍ ትብብር
8. የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ
   i. የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን (1992 እኤአ)፣ ፕሮቶኮሎች፣ ወዘተ፣ 2010 ጥቅምት 29 (እ.ኤ.አ)
   ii. የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን አባላት ጉባኤ (ናጕያ፣ ጃፓን፣ 2010 እ.ኤ.አ)
   iii. የተባበሩት መንግስታት
   ኬ3488-ኤ48 2011

ለተጨማሪ መረጃ የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ፅህፈት ቤትን ለመጠየቅ ይችላሉ፡፡

# መግቢያ

የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን በተባበሩት መንግስታት የአካባቢና ልማት ጉባኤ (የሪዮ "ኤርዝ ሰሚት") ለፊርማ ክፍት የተደረገው በሰኔ 5/1992 እ.ኤ.አ ሲሆን ተፈፃሚነቱ የፀናው ከታህሣሥ 29/1993 እ.ኤ.አ ጀምሮ ነው፡፡ ኮንቬንሽኑ የብዝሀ ሕይወትን በተመለከተ በስፋት የተዘጋጀ ብቸኛው የዓለም አቀፍ ሰነድ ነው፡፡

የኮንቬንሽኑ ሦስት አላማዎች፡- የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ፣ የብዝሃ ህይወት ሀብትን ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መጠቀም እና ከጀነቲክ ሀብት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ መካፈል ናቸው፡፡ የኮንቬንሽኑን ሶስተኛ አላማ ተግባራዊነትን የበለጠ ለማጠናከር በዘላቂ ልማት ላይ በተደረገ የአለም አቀፍ ጉባኤ (በጆሃንሰበርግ በመስከረም 2002 እ.ኤ.አ) የዓለም ሀገራት መንግስታት በኮንቬንሽኑ ማዕቀፍ ውስጥ ከጀነቲክ ሀብት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት ጥረት እንዲያደርጉ ጥሪ የተደረገበት ነው፡፡ የኮንቬንሽኑ አባላት ጉባኤ በ2004 እ.ኤ.አ በተካሄደው ሰባተኛ ስብሰባው የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪትን በተመለከተ የተቋቋመዉ ጊዜያዊ ኮሚቴበዓለም አቀፍ ደረጃ ውይይትና ድርድር በማካሄድ ኮንቬንሽኑና የኮንቬንሽኑ አንቀጽ 15 (የጀነቲክ ሀብት አርክቦት) እና 8 (በ) (ባህላዊ እውቀት) እና

የኮንቬንሽኑን ሶስቱንም አላማዎች በተሣካ ሁኔታ ለመተግበር እንዲቻል ስልጣን ሰጥቶታል፡፡

ከስድስት አመታት ድርድር በኋላ በጃፓን ሀገር በናጐያ ከተማ እ.ኤ.አ በጥቅምት 29/2010 በተደረገው የአባላት ጉባኤ አስረኛ ስብሰባ ላይ በጀነቲክ ሀብት አርክቦትና ሀብቱን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞች ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ስምምነት ላይ በመመርኮዝ የወጣ የናጐያ ፕሮቶኮል ሰነድ ተፈርሟል፡፡

ፕሮቶኮሉ ለጀነቲክ ሀብት አቅራቢዎች እና ተጠቃሚዎች የህግ ማዕቀፍ በማበጀትና ግልጽነት በማስፈን ጠንካራ መሠረት እንዲኖር በማድረግ ለኮንቬንሽኑ ሶስተኛው አላማ ተግባራዊነት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ጀነቲክ ሀብት የሚያቀርብ ወገን የውስጥ ሕጐችና መመሪያዎችን እንዲያከብር ወይም እንዲፈጽም የተቀመጡ ዝርዝር ግዴታዎች እና በጋራ በተደረሱባቸው ስምምነቶች ውስጥ የሚካተቱት የውል ግዴታዎች የፕሮቶኮሉ አይነተኛ ግኝቶችናቸዉ፡፡ እነዚህ ስምምነቶች እና ለጀነቲክ ሀብት አርክቦት ግልጽ እና ተገማች የሆኑ ሁኔታዎች እንዲኖሩ የተቀመጡ ደንቦች ጄኔቲክ ሀብቱ ከአቅራቢው ወገን ሲለይ ጥቅሞችን ለመጋራት በማስቻል ረገድ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዙ የአካባቢው ነዋሪዎች ወይም የማህበረሰቦች የባህላዊ

እውቀት፣ፈጠራ እና ልማድ አርክቦትን የሚመለከቱ የፕሮቶኮሉ ድንጋጌዎች እነዚህ ማህበረሰቦች የራሣቸው የሆነ እውቀት፣ፈጠራ እና ልማድ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችላቸውን አቅም ይፈጥሩላቸዋል፡፡

የጄኔቲክ ሀብት እና ተያያዥ ባህላዊ እውቀት አጠቃቀምን በማበረታተት እና እነዚህን ከመጠቀም የተነሣ የሚገኙሀብት ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት አመቺእድሎችን በማጠናከር ረገድ ፕሮቶኮሉ ማበረታቻ በመፍጠር ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃ፣ ተያያዥ ሀብትን ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እንዲሁም የብዝሀ ሕይወት ዘላቂነት ባለው ልማትና ለሰው ልጆች የተሻለ ኑሮ በመፍጠር ሂደት ውስጥ የላቀ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

# <u>የጀነቲክ ሀብት አርክቦት እና ሀብቱን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞች ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋራት በብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ላይ በመመርኮዝ የወጣ የናጎያ ፕሮቶኮል</u>

የፕሮቶኮሉ አባላት፡-

ከዚህ በኋላ “ኮንቬንሽን” ተብሎ የሚጠራው የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽንን የተቀበሉ አባላት በመሆናቸው፣

ጀነቲክ ሀብት በጥቅም ላይ ከመዋል ጋር በተያያዘ የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ መጋራት ከኮንቬንሽኑ ሶስቱ አላማዎች አንዱና ዋናው መሆኑን በመረዳት፣ የኮንቬንሽኑን ይህንን ዓላማ ለማስፈፀም የሚውል መሆኑን በመቀበል ሀገራት በኮንቬንሽኑ ውስጥ በተገለጸው መሠረት የተፈጥሮ ሀብታቸዉን ለመጠቀም ሉአላዊ መብቶች ያሏቸው መሆኑን ደግሞ በማረጋገጥ፣

የኮንቬንሽኑን አንቀጽ 15 ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣

በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 16 እና አንቀጽ 19 መሠረት በታዳጊ ሀገራት የጀነቲክ ሀብት ላይ ተጨማሪ ዕሴት ለመጨመር የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮች አቅም ለመገንባት በተደረገው ትብብር እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዘላቂነት ያለው ልማት እንዲኖር ያደረጉትን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በመረዳት፣

የስነምህዳር እና የብዝሀ ሕይወት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ዋጋ በተመለከተ አጠቃላይ ህብረተሰቡ ያለው ግንዛቤ እና ይህንን ጥቅም ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ከብዝሀ ህይወቱ ጠባቂ የማህበረሰብ አካላት ጋር የመጋራት ሁኔታ ለብዝሀ ህይወት ጥበቃና እንክብካቤ

እንዲሁም ተያያዥ ሀብቶችን ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመጠቀም ቁልፍ ማበረታቻ መሆናቸውን በመገንዘብ፣አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት በብዝሀ ህይወት ጥበቃና ዘለቄታዊ አጠቃቀም፣ ድህነትን ለማጥፋት እና የአካባቢ ዘለቄታዊነት ብሎም የምእተ-ዓመት ግቦችን ለማሣካት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚኖረውን ከፍተኛ ሚና እውቅና በመስጠት ፣በጀነቲክ ሀብት አርክቦት እና ፍትሐዊ እና ተመጣጣኝ የሆነ ጥቅም ተጋሪነት መካከል ያለውን ትስስር እውቅና በመስጠት ፣

የጀነቲክ ሀብት አርክቦትና ፍትሐዊና ተመጣጣኝ የሆነ ጥቅም ተጋሪነትን በተመለከተ አስተማማኝ የሆነ የህግ ስርአት እንዲኖር ማድረግ የሚኖረውን ጥቅም በመገንዘብ፣

በጀነቲክ ሀብት አቅራቢዎችና ተጠቃሚዎች መካከል የሚደረጉ ድርድሮች በጋራ የሚስማሙባቸውን ነጥቦች በሚመለከት ፍትሐዊነትና ተመጣጣኝነት እንዲጠናከር የማድረግ ሂደት ጠቀሜታን ይበልጥ በመገንዘብ፣

በአርክቦትና በጥቅም ተጋሪነት ውስጥ ሴቶች የሚጫወቱትን ወሣኝ ሚና በመረዳት የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ፖሊሲዎችን በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ውስጥ በሁሉም እርከኖች የሴቶችን ሙሉ ተሣትፎ በመገንዘብ፣

የኮንቬንሽኑን የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ድንጋጌዎችን ዉጤታማ አተገባበርን ለመደገፍ ቁርጠኛ በመሆን ፣

ከጀነቲክ ሀብት ጥቅም ላይ መዋል ጋር ተያይዘው የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ መጋራት እና ተያያዥ ባህላዊ የእውቀቶች አጠቃቀምን በተመለከተ የአስቀድሞ ተገንዝቦ እሺታ ሊገኝባቸው በማይችሉ ድንበር ተሻጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሲሆን ያለውን ሂደት በአግባቡ ለማስኬድ አዳዲስ መፍትሔዎች አስፈላጊ መሆናቸውን በመገንዘብ፣

የጀነቲክ ሀብት ለምግብ ዋስትና፣ ለህብተረሰብ ጤና፣ ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃና ፣ የአካባቢ አየር ንብረት ለውጥ ለመቀነስና ለመላመድ ፣

የግብርና-ነክ ብዝሀ ሕይወት ያለውን ለየት ያለ ሁኔታ፣ የተለያዩ ገጽታዎች እና ተያያዥ ችግሮች የተለያዩ መፍትሔዎችን የሚሹ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ጀነቲክ ሀብትን በተመለከተ በሁሉም ሀገራት መካከል ያለውን ትስስር በተለይም በምግብና በግብርና ረገድ የተሣሰሩ መሆናቸውን፣ እንዲሁም ከድህነት ቅነሣና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ባለው ሁኔታ ውስጥ በአለም አቀፍ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ያለው መሆኑን በመረዳት እና የእጽዋት ጀነቲክ ሀብትን የሚመለከተው አለም አቀፍ ስምምነት ለምግብና ለግብርና መሠረታዊ የሆነ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን፣

ከዚህ ጋር በተያያዘም በተባበሩት መንግስታት የምግብና የግብርና ኮሚሽን ያለውን ሚና በመረዳት፣

በተባበሩት መንግስታት የአለም የጤና ድርጅት ያወጣቸው አለም አቀፍ የጤና ደንቦች (2005) እና የህብረተሰብ ጤናን በማረጋገጥ ረገድ የሰው ልጆችን ጤና ለማረጋገጥና ዝግጁነት እንዲኖር ለማድረግ የሰው ልጆች የመዲሃኒቶች አርክቦት እንዲያድግ ማድረጉ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፣ አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነትን በተመለከተ ሌሎች በአለም አቀፍ ደረጃ እየተካሄዱ ያሉ ውይይቶች እውቅና በመስጠት ፣

የእጽዋት ጀነቲክስ ሀብት ለምግብና ለግብርና አለም አቀፍ ስምምነት ሥር የተዘጋጀው ባለብዙ ወገን የአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት ስርዓት ከኮንቬንሽኑ ጋር ተጣጥሞ የተዘጋጀ መሆኑን በማስታወስ፣

የኮንቬንሽኑን አላማዎች ለማሳካት የጀነቲክ ሀብትና ጥቅም ተጋሪነትን የሚመለከቱ ሰነዶች እርስ በእርሳቸው መደጋገፍ የሚገባቸው መሆኑን በመገንዘብ የኮንቬንሽኑ አንቀጽ 8(በ) ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዙ ባህላዊ እውቀቶች ጋር በተያያዘ እንዲሁም እነዚህን እውቀቶች በመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ያለውን ጠቀሜታ በማስታወስ፣

በጀነቲክ ሀብትና በባህላዊ እውቀት መካከል ያለውን ግንኙነት እና ከነባርና ከአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር ያላቸውን ተፈጥሯዊ ቁርኝት ፣

የባህላዊ እውቀት ለብዝሀሕይወት ጥበቃና ከነሱ የሚገኙትን ውጤቶች በዘላቂነት ለመጠቀም ፤ እንዲሁም የእነዚህን ማህበረሰቦች ኑሮ በዘላቂነት እንዲሻሻል ለማድረግ ፤

በነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ባለቤትነት ስር የሚገኙ ባህላዊ እውቀቶች ከጀነቲክ ሀብት ጋር በተያያዘ ያላቸውን የተለያዩ ሁኔታዎች በመገንዘብ፣

ከማህበረሰቦች መካከል ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዙ ባህላዊ እውቀቶች ባለሙሉ መብት የሆኑትን መለየት የነባርና የአካባቢው ማህበረሰቦች መብት መሆኑን በመረዳት፣

ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዙ ባህላዊ እውቀቶች በቃል፣ በሰነድ ወይም በሌሎች ዘዴዎች በሀገራት የተያዙ የተለዩ ሁኔታዎች ለብዝሃ ህይወት ጥበቃና ዘለቄታዊ አጠቃቀም አግባብነት ያላቸው የባህል ቅርስ ብልጽግና የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን የበለጠ በመረዳት፣

በተባበሩት መንግስታት የነባር ማህበረሰቦች መብቶች አዋጅ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ፕሮቶኮል ውስጥ ነባር ማህበረሰቦች ያሏቸውን መብቶች የሚቃረን ወይም የሚቀንስ ተደርጎ የማይተረጎም መሆኑን በማረጋገጥ እንደሚከተለው ተስማምተዋል ::

# አንቀጽ 1

# ዓላማ

የዚህ ፕሮቶኮል አላማ ጀነቲክ ሀብትን ከመጠቀም ጋር በተያያዘ የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሃዊና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ለመጋራት ማስቻል፣አግባብነት ያላቸውን የጀነቲክ ሀብት አርክቦትና ቴክኖሎጂዎችን በተገቢው መንገድ ማሸጋገርን ጨምሮ በነዚህ ሀብቶችና ቴክኖሎጂዎች ያሉትን መብቶች ግምት ውስጥ በማስገባት እና አስፈላጊውን ፈንድ በመመደብ ለብዝሃ ህይወት ጥበቃና ከነሱ የሚገኘውን ጥቅም በዘለቄታዊነት ለመጠቀም አስተዋፅኦ ማድረግ ነው፡፡

# አንቀጽ 2

# አተረጓጎም

በዚህ ፕሮቶኮል ውስጥ የተገለጹት ቃላት በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 2 ውስጥ የተሰጧቸው ትርጓሜዎች ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ፕሮቶኮል ውስጥ ቀጥሎ ያሉት ቃላት ከዚህ በታች የተሰጧቸው ትርጉሞች ይይዛሉ፡-

ሀ/ "የአባላት ጉባኤ" ማለት የኮንቤንሽኑ አባላት ጉባኤ ማለት ነው፡-

ለ/ "ኮንቬንሽን" ማለት የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ማለት ነው፡፡

ሐ/ "ጀነቲክ ሀብትን ጥቅም ላይ ማዋል" ማለት በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 2 ሥር ትርጓሜ የተሰጠውን ባዮቴክኖሎጂን ጨምሮ በጀነቲክ ሀብት ላይ ወይም በጀነቲክ ሀብት የባዮኬሚካል ቅይጥ ላይ ጥናትና ምርምር እንዲሁም ልማት ማካሄድ ማለት ነው፡፡

መ/ "ባዮቴክኖሎጂ" ማለት በስምምነቱ አንቀፅ 2 እንደተተረጎመው ማንኛውንም ቴክኖሎጂ ፣ስነ ህይወታዊ ስርዓት፣ህይወት ካላቸው ነገሮች ወይም የእነሱን ተዋፅኦ በመጠቀም በማሻሻልና በመስራት ለተለየ ጥቅም ለማዘጋጀት፡፡

ሠ/ "ተዋጽኦ" ማለት በተፈጥሮ የሚገኝ ከህይወታዊ ቅመም ወይም ከጀነቲክ ሀብት ተለይቶ የወጣ ወይም የተዘጋጀ ውጤት ሆኖ የዘረመል መሰረታዊ ህዋስ ቅንጅታዊ አሰራር ባይኖረዉም ይጨምራል፡፡

## <u>አንቀጽ 3</u>

## <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ፕሮቶኮል በኮንቬንሽኑ ስምምነት አንቀጽ 15 የተፈፃሚነት ወሰን መሠረት እና ከጀነቲክ ሀብት ጥቅም ላይ መዋል ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ጥቅሞችን በተመለከተ ተፈፃሚ ይሆናል ፡፡ በተጨማሪም ፕሮቶኮሉ በኮንቬንሽኑ የተፈፃሚነት ወሰን ውስጥ ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዙ ባህላዊ እውቀቶች ላይ ወይም / እና

እነዚህን እውቀቶች ጥቅም ላይ ከማዋል ጋር በተያያዘ የሚገኙ ጥቅሞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 4

## ከአለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሰነዶች ጋር ያለው ግንኙነት

1. በዚህ ፕሮቶኮል ውስጥ የተካተቱት አንቀፆች በአለም አቀፍ ስምምነት መሠረት የተገኙ የማንኛውንም አባል መብቶች እና ግዴታዎች ላይ ተግባራዊ ማድረጉ በብዝሃ ህይወት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ እስካልሆነ ድረስ ተጽእኖ አይኖራቸውም፣ ይህ አንቀጽ በዚህ ፕሮቶኮልና በሌሎች አለም አቀፍ ስምምነቶች መካከል የደረጃ ልዩነት ለመፍጠር የታሰበ አይደለም፡፡
2. ከዚህ ፕሮቶኮልና ከኮንቬንሽኑ አላማዎች ጋር ደጋፊ እስከሆኑና ተፃራሪ እስካልሆኑ ድረስ የዚህ ፕሮቶኮል አባላት ሌሎች የተለዩ አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነትን ስምምነቶችን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸው አለም አቀፋዊ ስምምነቶችን ከማዘጋጀት እና ተግባራዊ ከማድረግ የሚያግዳቸው ነገር አይኖርም፡፡
3. ይህ ፕሮቶኮል ከዚህ ፕሮቶኮል ጋር አግባብነት ያላቸው ሌሎች የአለም አቀፍ ሰነዶች ጋር በመደጋገፍ ተግባራዊ

ይሆናል፡፡ ከነዚህ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስር እየተተገበሩ ያሉ ስራዎች ወይም ተግባራት ከኮንቬንሽኑ እና ከፕሮቶኮሉ ዓላማዎች ጋር ተደጋጋፊ እስከሆኑና ተቃራኒ እስካልሆኑ ድረስ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

4. ይህ ፕሮቶኮል አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት የሚመለከቱ የኮንቬንሽኑ አንቀጾችን ለማስፈፀም የተዘጋጀ ሰነድ ነው፡፡ ከዚህ ፕሮቶኮልና ከኮንቬንሽኑ አላማዎች ጋር የማይቃረንና የተጣጣመ የተለየ አለም አቀፋዊ አርክቦትና ከጥቅም ተጋሪነት ሰነድ ጋር በተያያዘ ተግባራዊ በሚሆንበት ሁኔታ ውስጥ የተለዩ ጀነቲክ ሀብቶችን በተመለከተ ልዩ ሰነድ በተቀበለ አባል ወይም አባላት ላይ ይህ ፕሮቶኮል ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 5

## ፍትሐዊና ተመጣጣኝ የሆነ የጥቅም ተጋሪነት

1. በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 15 (ቁጥር 3 እና 7) መሠረት ጀነቲክ ሀብት ከመጠቀም ጋር ተያይዘው የሚገኙ ጥቅሞች እና ቀጣይ የአርክቦት ማመልከቻዎች እና ለንግድ የማዋል ሂደት ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ በጄነቲክ ሀብቱ መገኛ

ሀገር ወይም በኮንቬንሽኑ መሰረት የጄነቲክ ሀብቱ ያገኘ ወገን መካከል ይሆናል፡፡ መጋራቱም ሁለቱ በተስማሙባቸው የጋራ ነጥቦች መሰረት ይሆናል፡፡

2. እያንዳንዱ አባል ሀገር በነባርና በአካባቢ ማህበረሰቦች ከተያዘ ጀነቲክ ሀብት የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ ሲባል በሀገር ውስጥ ህጎች የተፈጠሩ የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች በጀነቲክ ሀብቶች ላይ ያላቸው መብት ሚዛናዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ በሚመለከታቸው ማህበረሰቦች መሀል በጋራ ተስማምተው ባስቀመጧቸው ነጥቦች መሰረት ለመጋራት እንዲቻል አግባብነት ያላቸውን የሕግ፣ አስተዳደራዊ ወይም የፖሊሲ እርምጃዎችን መዉሰድ ይኖርበታል፡፡
3. ከዚህ በላይ የተገለጸውን አንቀጽ (1) ተፈፃሚ ለማድረግ እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል አግባብነት ያላቸው የሕግ፣ አስተዳደራዊ ወይም የፖሊሲ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
4. ጥቅሞች የሚባሉት ገንዘብ-ነክ ወይም ገንዘብ-ነክ ያልሆኑና በአባሪ ሰነድ ውስጥ የተዘረዘሩትን የሚያጠቃልል ነገር ግን በእነሱ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡
5. እያንዳንዱ ወገን ከጀነቲክ ሀብት ጋር በተያያዘ የባህላዊ እውቀትን ከመጠቀም የሚገኘውን ጥቅም ፍትሃዊና

ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ከእውቀቱ ባለቤቶች ከሆኑ ነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር ለመጋራት አግባብነት ያላቸውን ህጋዊ፣አስተዳደራዊና የፖሊሲ እርምጃዎችን ይወስዳል ክፍፍሉም ሁለቱ ወገኖች በተስማሙባቸው የጋራ ነጥቦች መሰረት ይሆናል፡፡

## <u>አንቀጽ 6</u>

## <u>የጀነቲክ ሀብት አርክቦት</u>

1. በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ያለን ሉአላዊ መብት እና በሀገር ውስጥ የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ህጎች ወይም የቁጥጥር ቅድመ ሁኔታዎች ተግባራዊ በማድረግ የጀነቲክ ሀብት ለመጠቀም አርክቦት ለማግኘት የሀብቱን አቅራቢ ወገን ማለትም የሀብቱ መገኛ ሀገር ወይም የጀነቲክ ሀብቱን በኮንቬንሽኑ መሰረት ያገኘ ወገን በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር የዚሁ አካል አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
2. እያንዳንዱ አባል በሀገሩ ሕግ መሠረት የጀነቲክ ሀብት አርክቦት ለመስጠት መብት ያላቸው ነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ሲኖሩ ከእነዚህ ማህበረሰቦች አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ወይም ተቀባይነት እና

ተሳትፏቸውን የሚያረጋግጡ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

3. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 ሥር በተገለፀው መሠረት አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የሚፈልግ ማንኛውም አባል ከዚህ በታች የተገለጹትን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የሕግ፣ አስተዳደራዊ ወይም የፖሊሲ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል፡-

ሀ/ የሀገር ውስጥ አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነትንየሚመለከቱ ሕጐችና አስተዳደራዊ መስፈረቶች ትክክለኛ ፣የጠሩና ግልፅ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

ለ/ የጀነቲክ ሀብት አርክቦትን በተመለከተ ፍትሐዊ እና ዘፈቀዳዊ ያልሆኑ መመሪያዎችና ስነስርአቶች እንዲኖሩ ያደርጋል ፣

ሐ/ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ለማግኘት እንዴት መጠየቅ እንደሚገባ መረጃ ይሰጣል ፣

መ/ በተገቢው ብሄራዊ ባለስልጣን የሚሰጡ ውሳኔዎች ግልፅ ና የማያሻሙ እንዲሁም በተገቢው የጊዜ ገደብና ወጭ በጽሁፍ እንዲሰጡ ማድረግ፣

ሠ/ በአርክቦት ጊዜ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ለመስጠት ለተወሰነ ውሣኔ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ፈቃድ እንዲሰጥ ማድረግና በዚሁ መሠረት ለአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት ማሳወቅ፣

የአርክቦት ወይም ይህንን የመሰለ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ እና በጋራ የተስማሙባቸው ነጥቦች ውሳኔ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ለአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት ማሳወቅ፣

ረ/ ተፈፃሚነት ያለው ሆኖ ሲገኝ እና በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ሊታይ የሚችል ሲሆን አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ወይም እውቅና ወይም የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች በአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ውስጥ ተሳትፏቸውን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መሥፈርቶች እና ወይም ሂደቶች ማዘጋጀት ፣

ሰ/ የጋራ ስምምነቶችን የሚጠይቁ እና የሚያቋቋሙ ግልፅ መመሪያዎችና ስነስርዓቶችን ማስቀመጥ ላይ ለመድረስ የሚረዱ እና መሟላት የሚገባቸው ግልጽ መመሪያዎችና ስነስርአቶችን ማስቀመጥ፡፡ እነዚህ ስነስርአቶች እና

መመሪያዎች በጽሑፍ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሚከተሉትን ሊያካተቱ ይችላሉ፡-

1. የግጭት መፍቻ አንቀፅ፣
2. የጥቅም ተጋሪነት መመሪያዎች፣ የአእምሯዊ ንብረት መብቶችን ጨምሮ ፣
3. በቀጣይነት ሦስተኛ ወገን (ካለ) ሊጠቀምበት የሚችልበትን ሁኔታ የሚመለከቱ መመሪያዎች እና
4. ተፈፃሚነት ያለው ከሆነ ሀሣብ መለወጥን የሚመለከቱ መመሪያዎች፣

## አንቀጽ 7

## ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዥ ባህላዊ እውቀት አርክቦት

የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥ የሆኑ ባህላዊ እውቀቶች አርክቦት በነባርና የአካባቢ ማህበረሰብ አስቀድሞ ተገንዝቦ በሚሰጥ እሽታ ወይም እውቅናና ተሳትፎ እንዲሁም የጋራ መግባቢያ ነጥቦችን በማስቀመጥ እንዲሆን እያንዳንዱ ወገን በሀገሩ የውስጥ ህጎች መሰረት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

# አንቀጽ 8

## ልዩ ትኩረቶች

እያንዳን ወገን አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት የሚመለከቱ ሕጐችና አስተዳደራዊ መመሪያዎችን በማዘጋጀትና በመተግበር ሂደት ውስጥ ከዚህ በታች የተገለፁትን ማከናወን ይኖርበታል፡-

ሀ/ ብዝሀ ህይወትን ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ጥናትና ምርምሮችን ማነሳሳትና ማበረታታት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን መፍጠር ፣ በተለይም በማደግ ላይ ባሉ ሐገራት ጥናትና ምርምር የሚካሄድባቸው አላማዎች መቀያየርን ከግምት ውስጥ በማስገባት አርክቦትና ለንግድ አላማ ያልሆኑ የጥናትና ምርምር ተግባራትን እንዲከናወኑ የሚያስችሉ ቀለል ያሉ እርምጃዎችን መውሰድ፣

ለ/ በሀገርአቀፍ ወይም ዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ በሰወች፣በእንስሳት ወይም በእፅዋት ጤና ላይ ድንገተኛ ስጋት ወይም ጉዳት የሚያደርሱ ወቅታዊ ወይም የቀረበ ድንገተኛ አደጋወችን በተመለከተ ተገቢውን ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡

አባል ሀገራት ፈጣን የጀነቲክ ሀብት አርክቦትና ከጀነቲክ ሀብት መጠቀም የሚገኘውን ጥቅም ፈጣን በሆነ ሁኔታ ፍትሀዊና ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ የመጋራትን አስፈላጊነት

እንዲሁም በተለይ በታዳጊ ሀገራት ውስጥ ህክምናውን ለሚፈልጉ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ትኩረት ማድረግ አለባቸው።

ሐ/ ጀነቲክ ሀብት ለምግብና ለግብርና ያላቸውን ጠቀሜታ በተለይም ለምግብ ዋስትና ያላቸውን ልዩ ሚና ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

## አንቀጽ 9

## ለጥበቃና ለዘላቂ አጠቃቀም አስተዋጽኦ ማድረግ

አባል ሀገራት የጀነቲክ ሀብትን ጥቅም ላይ ከማዋል የሚገኙ ጥቅሞችን ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃ እና ከነሱ የሚገኘውንም ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መጠቀም ወደሚያስችሉ ጥቅሞች እንዲያተኩሩ ተጠቃሚዎችንና አቅራቢዎችን ማበረታታት ይኖርባቸዋል።

## አንቀጽ 10

## ዓለም አቀፋዊ ባለብዙ ወገን ጥቅም ተጋሪነት ዘዴ

አባል ሀገራት ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ወይም አስቀድሞ ተገንዝቦ እሺታን ለማግኘት ወይም ለመስጠት አዳጋች የሆኑ የጀነቲክ ሀብት እና ተያያዥ ባህላዊ እውቀት አርክቦትና ፍትሐዊና ተመጣጣኝ ጥቅም ተጋሪነት የሚፈፀምበት አለም አቀፍ ባለ ብዙ ወገን ጥቅም

ተጋሪነት ስርአት መዘርጋት አስፈላጊነትን መገንዘብ አለባቸው፡፡በዚህ ሂደት የጀነቲክ ሀብትና ተያያዥ ባህላዊ እውቀትን ከመጠቀም የሚገኙ ጥቅሞች በአለም አቀፍ ብዝሀ ሕይወትን እና ክፍሎቹን ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም መዋል አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 11

## ድንበር-ተሻጋሪ ትብብር

1. ተመሣሣይ የሆነ ጀነቲክ ሀብት ከአንድ በላይ በሆኑ አባል ሀገራት ድንበር ውስጥ በዘቦታ የሚገኝ ከሆነ እነዚህ አባላት እንደአስፈላጊነቱ የሚመለከታቸው ነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ተሣትፎ እንዲኖር በማድረግ ለዚህ ፕሮቶኮል ተፈፃሚነት በጋራ ተባብሮ ለመሥራት ጥረት ያደርጋሉ፡፡
2. ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዘ አንድ አይነት ባህላዊ እውቀት ከአንድ በላይ በሆኑና በተለያዩ ሀገራት በሚገኙ የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች የሚጋሩት ከሆነ የእነዚህ ሀገራት እንደአስፈላጊነቱ የሚመለከታቸው ነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ተሣትፎ እንዲኖር ጥረት በማድረግ ለዚህ ፕሮቶኮል ተፈፃሚነት ይተባበራሉ፡፡

# አንቀጽ 12

# ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥ ባህላዊ እውቀት

1. በዚህ ፕሮቶኮል መሠረት ያሉባቸውን ግዴታዎች በመፈፀም በፕሮቶኮሉ አባል ሀገራት የውስጥ ሕጐች መሠረት የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ባህላዊ ሕጐች፣ ፕሮቶኮሎች እና ስነስርአቶችን ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዙ የባህላዊ እውቀቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
2. አባል ሀገራት ከሚመለከታቸው የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ንቁ ተሣትፎ ባለበት ሁኔታ ከጀነቲክ ሀብት ጋር በተያያዘ የባህላዊ እውቀት ዋና ተጠቃሚዎችን ስለግዴታዎቻቸው ለማሳወቅ ስልት ማበጀት፣ለማርከብና ባህላዊ እውቀትን ከመጠቀም የሚገኘውን ጥቅም ፍትሀዊና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ለመጋራት የሚወሰዱ እርምጃዎችን በአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት በኩል እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
3. የፕሮቶኮሉ አባላት እንደ አስፈላጊነቱ የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦችና በእነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን ጨምሮ ከዚህ በታች የተገለጹትን በማከናወን ሂደት ውስጥ ድጋፍ ለመስጠት ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡-

ሀ/ ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥ የሆነ ባህላዊ እውቀት አርክቦትን እና ከዚሁ እውቀት የሚገኙ ፍትሀዊና ተመጣጣኝ ጥቅሞችን የሚመለከት የማህበረሰብ ፕሮቶኮል ማዘጋጀት፣

ለ/ ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥነት ያለው ባህላዊ እውቀት ከመጠቀም ጋር በተገናኘ የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ መጋራትን ለማስጠበቅ የጋራ ስምምነቶች ማሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ መሥፈርቶች፣

ሐ/ ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥ የሆነ ባህላዊ እውቀት ከመጠቀም ጋር በተያያዘ የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሐዊና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ለመጋራት የሚደረጉ ሞዴል የውል ሀረጎች ፣

4. ይህንን ፕሮቶኮል ተፈፃሚ በማድረግ ሂደት ውስጥ የፕሮቶኮሉ አባላት በተቻለ መጠን በኮንቬንሽኑ አላማዎች መሠረት በነባርና በአካባቢ ማህበረሰቦች በራሳቸውና በማህበረሰቦች መካከል ጀነቲክ ሀብትና ተያያዥ ባህላዊ እውቀትን የመለዋወጥና የመጠቀም ልማዳዊ አሰራሮችን አይገደቡም፡፡

# አንቀጽ 13

## ብሔራዊ ተጠሪ መስሪያ ቤት እና ባለስልጣን አካላት

1. እያንዳንዱ አባል ብሄራዊ የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ተጠሪ መስሪያ ቤት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ብሄራዊ ተጠሪ መስሪያ ቤቱም በሚከተለው መንገድ ያደርጋል ፡-

ሀ/ የጀነቲክ ሀብት አርክቦት ለማግኘት፣ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የሚገኝበትን ስነስርዓት በተመለከተ፣ የጋራ ስምምነቶች የሚደረጉባቸው ሁኔታዎች የጥቅም ተጋሪነትን ጨምሮ መረጃ ማግኘት ለሚፈልጉ አመልካቾች፣

ለ/ ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥ ለሆነ ባህላዊ እውቀት አርክቦት ለሚፈልጉ አመልካቾች አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የማግኘት ስርዓት ወይም የማፅደቅና ፣ የጋራ መግባቢያ ሰነድ ዝግጅት እና ጥቅም ተጋሪነትን ጨምሮ የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ተሣትፎ ባለበት መንገድ የሚገኝበትን መረጃ መስጠት፣

ሐ/ ብሄራዊ ባለስልጣን አካላትን፣ የሚመለከታቸው ነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦችን እና ባለድርሻ አካላትን የሚመለከቱ መረጃዎች፣ብሄራዊ ተጠሪ መስሪያ ቤቱ ከፅህፈት ቤቱ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን በማከናወን ረገድ ኃላፊነት አለበት ፡፡

2. እያንዳንዱ አባል ሀገር በአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ላይ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ብሄራዊ ባለስልጣን ሊወክሉ ይገባል፡፡

ብሄራዊ ባለስልጣናት ተፈጻሚነት ባላቸው ብሄራዊ ህጎች፣አስተዳደራዊ ወይም የፖሊሲ ርምጃዎች መሰረት አርክቦት የመስጠት ኃላፊነት ወይም የአርክቦት መስፈርቶችን ሲያሟሉ የፅሁፍ ማስረጃ የመስጠት እና በአፈፃፀም ስርዓቶች እና አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች እና የጋራ መግባቢያ ሠነዶች የመዋዋል ላይ ምክር የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3. አንድ አባል የብሄራዊ ባለስልጣን አካል እና ተጠሪ መስሪያ ቤት ኃላፊነቶችን የሚወጣ አንድ አካል ሊያቋቁም ይችላል፡፡
4. ይህ ፕሮቶኮል ተፈፃሚ መሆን ከሚጀምርበት ቀን አስቀድሞ እያንዳንዱ አባል የተጠሪ መስሪያ ቤቱን እና በብሔራዊ ደረጃ ስልጣን ለተሰጠው አካል ወይም አካላት የሚገኙበትን አድራሻ ለፅህፈት ቤቱ ያሳውቃል፡፡ አንድ አባል ሀገር ከአንድ በላይ የሆኑ ተጠሪ መስሪያ ቤትና ባለስልጣን አካላት ያለው ከሆነ የእነዚህን አካላት ኃላፊነቶች በተመለከተ ለፅህፈት ቤቱ ያሳውቃል ፡፡ ተፈፃሚነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ይህ መረጃ

ቢያንስ የትኛው ባለስልጣን ጀነቲክ ሀብትን በተመለከተ ኃላፊነት እንዳለበት የሚገለጽ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ በኋላም እያንዳንዱ አባል ሀገር ተጠሪ መስሪያ ቤትና የባለስልጣን አካላቱን በተመለከተ የሚኖሩ ማንኛውንም ለውጦች ለፅህፈት ቤቱ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት ፡፡

5. ፅህፈት ቤቱ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 4 ሥር በተገለጸው መሠረት የሚገኙትን መረጃዎች በአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት በኩል ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 14

## የአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት እና የመረጃ ልውውጥ

1. የአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 18 /ተራ ቁጥር 3/ ሥር የተገለፀው የአጣሪ ምክር ቤት አሰራር አካል ሆኖ ተቋቁሟል፡፡ምክር ቤቱ አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያገለግል አካል ይሆናል፡፡ በተለይም ፕሮቶኮሉን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር በተያያዘ በአባል ሀገራት የሚቀርቡ መረጃዎች ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

2. በምስጢር የሚያዙ መረጃዎችን በተመለከተ ያሉት መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆኖ እያንዳንዱ አባል ሀገር ማንኛውንም መረጃ እንዲሁም እያንዳንዱ የአባል ሀገራት ጉባኤ ውሳኔዎችን ተከትሎ ለዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ አገልግሎት እንዲቀርቡ የተወሰኑ መረጃዎችን ለአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት ተደራሽ ያደርጋል ፡፡ እነዚህ መረጃዎችም፡-

ሀ/ አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነትን በተመለከተ ያሉ የሕግ፣ አስተዳደራዊ ወይም የፖሊሲ እርምጃዎች፣

ለ/ በብሄራዊ ደረጃ የተቋቋሙ ሀገራዊ ተጠሪ መስሪያ ቤትና ባለስልጣን አካል ወይም አካላት የሚመለከቱ መረጃዎችን፣ እና

ሐ/ በአርክቦት ወቅት የሚሰጡ ፍቃዶች ወይም ተመጣጣኛቸው አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታና የጋራ ስምምነት ነጥቦች ለማቋቋም የተሰጡ ውሳኔዎችን የሚያስረዱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

3. ከዚህ በታች የተመለከቱ ተጨማሪ መረጃዎች የሚኖሩ ከሆነ እና አስፈላጊ ከሆኑ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል ፡-

ሀ/ ነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች አግባብነት ያላቸው ባለስልጣናት እና ተያያዥ መረጃዎች፣

ለ/ ሞዴል የውል አንቀፆች፣

ሐ/ የጀነቲክ ሀብቶችን በተመለከተ ክትትል ለማድረግ የተዘጋጁ ዘዴዎችና መሳሪዎች እና

መ/ የሥነ ምግባር መመሪያዎች እና መልካም ተሞክሮዎች

4. የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት ያከናወናቸው ተግባራት ሪፖርቶችን ማዘጋጀት ጨምሮ ኃላፊነቶቹን የሚወጣበት የአሰራር መመሪያዎች በአባል ሐገራት የመጀመሪያ ጉባኤ ላይ በሚወሰነው እና ከዚያ በኋላ በተለያዩ ወቅቶች በሚሻሻልበት መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 15

## አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት የሚመለከቱ የሀገር ውስጥ ሕጐች ወይም ደንቦችንስለማክበር

1. እያንዳንዱ አባል/ሀገር በግዛቱ ውስጥ ጥቅም እየሰጠ ያለ የጀነቲክ ሀብት አርክቦት በሀገሩ የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ህጎች በሚያዙት መሰረት አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የተገኘበትና የጋራ መግባቢያ ሰነድ የተዘጋጀበት ወይም የሌላኛው ሀገር የቁጥጥር ቅድመ ሁኔታ ያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢ፣ውጤታማ እና ተመጣጣኝ የሕግ፣አስተዳደራዊና ፖሊሲያዊ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

2. አባል ሀገራት ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 በተገለጸው አንቀጽ መሠረት የተወሰዱ እርምጃዎችን ያለማክበር ሁኔታዎችን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው፣ ውጤታማና ተመጣጣኝ እርምጃዎች ይወስዳሉ፡፡
3. አባል ሀገራት በተቻለ መጠን እና እንዳስፈላጊነቱ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 ሥር የተገለጸውን የሀገር ውስጥ አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት ሕጎችን ወይም የቁጥጥር ቅድመ ሁኔታዎችን ያለማክበር ሁኔታ ሲኖር በጋራ መተባበር ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 16

## ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዘ ባህላዊ እውቀት አርክቦት እና የጥቅም ተጋሪነት የሚመለከቱ የሀገር ውስጥ ሕግ ወይም ደንቦችን ስለማክበር

1. እያንዳንዱ ወገን በድንበሩ ውስጥ በጥቅም ላይ የሚውል ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥ የሆነ ባህላዊ እውቀት አስቀድሞ ተገንዝቦ በሚሰጥ እሽታ ወይም ይሁንታ እና በነባርና በአካባቢ ማህበረሰቦች ተሣትፎ እና የጋራ ስምምነት ተቋቁሞ አርክቦት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸውን ውጤታማና ተመጣጣኝ የሕግ፣ አስተዳደራዊ ወይም የፖሊሲ እርምጃዎች ይወስዳል፡፡ እንዲሁም ነባሮችና የአካባቢው ማህበረሰቦች የሚገኙበት ሌላኛው ወገን በሀገር ውስጥ

የአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት ህጎች ወይም አስተዳደራዊ ቅድመ ሁኔታዎችን በሚጠይቁት መሠረት የጋራ ስምምነቶች መደረጋቸውን ያረጋግጣል፡፡

2. እያንዳንዱ የፕሮቶኮሉ አባል ሐገራት ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 ሥር በተገለጸው መሠረት የተወሰዱ እርምጃዎች ተግባራዊ ሣያደርጉ ሲቀሩ አግባብነት ያላቸው ውጤታማና ተመጣጣኝ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

3. የፕሮቶኮሉ አባል ሀገራት በተቻለ መጠን እና እንደ አስፈላጊነቱ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 ሥር የተገለፁት የሀገር ውስጥ የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ህግ ወይም አስተዳደራዊ ቅድመ ሁኔታዎች ሲጣሱ ሊተባበሩ ይገባል፡፡

## <u>አንቀጽ 17</u>

## <u>የጀነቲክ ሀብት አጠቃቀም ክትትል</u>

1. እያንዳንዱ ወገን የጀነቲክ ሀብት አጠቃቀምን በተመለከተ ክትትል ማድረግ እና ግልጽነት እንዲሰፍን አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች በመውሰድ ለተግባራዊነቱ ድጋፍ ለማድረግ ይኖርበታል፡፡እርምጃዎቹም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ/ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የፍተሻ ኬላዎችን ማቋቋም፡-

1. የፍተሻ ኬላዎች እንደአስፈላጊነቱ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ፣ የጀነቲክ ሀብቱን ምንጭ፣የጋራ መግባቢያ ሰነዶች መደረጋቸው እና/ወይም የጀነቲክ ሀብት አጠቃቀም የሚመለከቱ መረጃዎች ይቀበላሉ ወይም ይሰበስባሉ፡፡
2. እያንዳንዱ አባል እንደ አግባብነቱ እና በተመደበው የፍተሻ ኬላ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ በመመስረት የጀነቲክ ኬላ የጀነቲክ ሀብት ተጠቃሚዎች በተመደበው የፍተሸ ኬላ ከዚህ በላይ የተገለፁ መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ይጠይቃል፡፡ እያንዳንዱ አባል ተግባራዊ ያለማድረግ ሁኔታ ሲፈጠር አግባብነት ያላቸው፣ውጤታማና ተመጣጣኝ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
3. እነዚህ መረጃዎች በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸው ተግባራዊ ማድረግን የሚመለከቱ የምስክር ወረቀቶች ወይም ማስረጃዎች ጨምሮ የመረጃ ሚስጢር የመጠበቅ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሚመለከተው ብሄራዊ ባለስልጣን አካላት፣ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ለሚሰጥ ወገን፣ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ለአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት የሚቀርቡ ይሆናል፡፡
4. የፍተሻ ኬላዎች ውጤታማና በአግባቡ ተግባሮቻቸውን የሚያከናውኑ እና የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (ሀ)ን

ለመተግበር የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸውን ተግባራት የሚያከናውኑ መሆን ይኖርባቸዋል። ከጀነቲክ ሀብት አጠቃቀም ጋር አግባብነት ያላቸው ወይም በማንኛውም ደረጃ ላይ ያሉ የምርምር ሥራዎች ለልማት፣ለፈጠራ፣ለንግድ አላማ ወይም ለቅድመ ንግድ የሚውሉ ተገቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያገለግሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

ለ/ የጀነቲክ ሀብት አቅራቢዎችና ተጠቃሚዎች በጋራ በሚያደርጓቸው ስምምነቶች ውስጥ እነዚህን ስምምነቶች ለመተግበር መረጃዎችን ለመጋራት፣ሪፖርት የማድረግ ቅድመ ሁኔታን ጨምሮ ፣የመረጃ ልውውጥን የሚመለከቱትን እንዲያካትቱ ማበረታታት፣

ሐ/ ወጪ ቆጣቢ የመገናኛ ዘዴዎችና ሥርአቶችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማበረታታት።

2. በአንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 3(ረ) ሥር በተገለጸው መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ወይም ተመሳሳዩ ከአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት የሚገኝ ማስረጃ በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው ተግባራዊ የሚድረግ ማስረጃ ሆኖ የሚወሰድ ይሆናል።
3. በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የምስክር ወረቀት የሚመለከተው የጀነቲክ ሀብት አርክቦት አስቀድሞ ተገንዝቦ

በሚሰጥ እሽታ እና የጋራ ስምምነቶች መሠረት በሀገር ውስጥ የአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት መመሪያዎች ወይም በአስቀድሞ ተገንዝቦ እሽታ ሰጭው የቁጥጥር ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት ለመካሄዳቸው ማስረጃ ይሆናል፡፡

4. በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የተሟላ ምስክር ወረቀት በምስጢር የሚያዙ ካልሆኑ በስተቀር የሚከተሉትን አነስተኛ መረጃዎች ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ/ የሰጠው ባለስልጣን፣

ለ/ የተሰጠበት ቀን፣

ሐ/ አቅራቢው፣

መ/ የምስክር ወረቀቱ ልዩ መለያ፣

ሠ/ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ የተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት፣

ረ/በምስክር ወረቀቱ የተካተቱት ጀነቲክ ሀብቶች ወይም ጉዳይ፣

ሰ/ የጋራ ስምምነት ስለመደረጉ ማረጋገጫ፣

ሸ/ አስቀድሞ ተገንዝቦ የሚሰጥ እሽታ ለመገኘቱ ማረጋገጫ እና

ቀ/ ለንግድ-ነክ እና/ወይም ንግድ-ነክ ላልሆነ ጥቅም መሆኑን ፡፡

# አንቀጽ 18

## የጋራ ስምምነቶችን ተግባራዊ ስለማድረግ

1. የዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 6፣ ተራ ቁጥር 3 /ሰ/ /ቀ/ እና አንቀጽ 7 ተግባራዊ ሲደረጉ ውስጥ እያንዳንዱ አባል የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዘ ባህላዊ እውቀት አቅራቢዎችና ተጠቃሚዎች ከዚህ በታች የተገለፁትን ጨምሮ የአለመግባባት አፈታት አንቀጾችን በጋራ ስምምነቶች ውስጥ እንደ አስፈላጊነታቸው እንዲያካትቱ ማበረታታት አለበት፡፡

   ሀ/ ማንኛውንም አለመግባባት የተፈጠረበትን ጉዳይ የማየት ስልጣን ያለው አካል፣

   ለ/ ገዥ ሕግ፣ እና/ ወይም

   ሐ/ የግልግል ዳኝነት እና ስምምነትን የመሳሰሉ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን

2. እያንዳንዱ አባል በጋራ የተደረጉ ስምምነቶችን በተመለከተ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ተፈፃሚነት ባለው ሕግ መሠረት በሀገራቸው የሕግ ስርአት ውስጥ ካሳ የመጠየቅ እድል ያለ መኖሩን ያረጋግጣል፡፡
3. እያንዳንዱ አባል ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎችን ይወስዳል :-

ሀ/ ፍትህ የማግኘት እና

ለ/ በውጪ አገር የተሰጡ ውሳኔዎችንና እና የግልግል ዳኝነትን የማስፈፀምና በጋራ እውቅና መስጠትን በተመለከተ የማስፈፀሚያ ዘዴዎች የመጠቀም

4. የዚህ አንቀጽ ውጤታማነት በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 31 መሠረት በፕሮቶኮሉ አባል ሀገራት ጉባኤ በሚያገለግለው የአባል ሀገራት ስብሰባ የሚገመገም ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 19

## ሞዴል የውል አንቀጾች

1. የጋራ ስምምነቶች በተመለከተ እያንዳንዱ አባል ሀገር የሴክተር እና በሴክተሮች መካከል ክሮስ ሴክተር ሞዴል የውል ሀረጎች እንደ አግባብነታቸው በማዘጋጀት በማሻሻልና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያበረታታል፡፡
2. የዚህ ፕሮቶኮል አባላት ጉባኤ በመሆን የሚያገለግሉ የአባላት ስብሰባ በየጊዜው የሴክተር እና በሴክተሮች መካከል ሞዴል የውል አንቀፆች አገልግሎት ላይ የማዋል ስቶክ(stock) ይወስዳል፡፡

## አንቀጽ 20

## የሥነ ምግባር መርሆች፣ መመሪያዎች እና መልካም ተሞክሮዎች እና /ወይም ደረጃዎች

1. እያንዳንዱ አባልሀገር አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነትን በተመለከተ በራሳቸው ተነሳሽነት የስነ ምግባር መርሆዎች፣መመሪያዎችና መልካም ተሞክሮዎች እና/ወይም ደረጃዎች እንዲዘጋጁ፣እንዲሻሻሉና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማበረታታት አለባቸው፡፡
2. የዚህ ፕሮቶኮል አባላት ጉባኤ በመሆን የሚያገለግሉ የአባላት ስብሰባ በየወቅቱ የስነ ምግባር መርሆች፣ መመሪያዎች እና መልካም ተሞክሮዎች እና/ወይም ደረጃዎችን የመጠቀም እንዲሁም የተወሰኑ የሥነ ምግባር መርሆች፣ መመሪያዎች እና መልካም ተሞክሮች እና/ወይም ደረጃዎች ቀምሮ የመጠቀም ሁኔታን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ፡፡

## አንቀጽ 21

## ግንዛቤ ማሳደግ

እያንዳንዱ አባል ጀነቲክ ሀብትና ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዘ ባህላዊ እውቀት እንዲሁም ተያያዥ የሆኑ የአርክቦትና የጥቅም

ተጋሪነት ጉዳዮች አስፈላጊነት በተመለከተ ግንዛቤ ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

እነዚህ እርምጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ/ ይህንን ፕሮቶኮልና አላማዎቹን ማስተዋወቅ፣

ለ/ ነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች እና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ስብሰባዎችን ማዘጋጀት ፣

ሐ. ለነባርና ለአካባቢ ማህበረሰቦችና እንዲሁም ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ድጋፍ የሚሰጥ ዴስክ ማቋቋምና ማጠናከር፣

መ/ በብሄራዊ አጣሪ ምክር ቤት አማካኝነት መረጃዎችን ማሰራጨት፣

ሠ/ ከነባርና ከአካባቢ ማህበረሰቦችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር የበጎ ፈቃድ ሥነ ምግባር መርሆችን፣ መመሪያዎች እና መልካም ተሞክሮዎች እና/ ወይም ደረጃዎችን ማስተዋወቅ፣

ረ/ እንደ አግባብነታቸው ሀገራዊ፣አህጉራዊና አለም አቀፋዊየልምድ ልውውጥን ማስተዋወቅ፣

ሰ/ የጀነቲክ ሀብትና ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥ ባህላዊ እውቀት ተጠቃሚዎች እና አቅራቢዎች አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነታቸውን በተመለከተ ባሉባቸው ግዴታዎች ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣

ሸ/ ይህንን ፕሮቶኮል ተግባራዊ በማድረግ ውስጥ የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦችና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ተሣትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

ቀ/ የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች ፕሮቶኮሎችና አሰራሮችን በተመለከተ ግንዛቤ ማሳደግ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 22

## አቅም

1. አባል ሀገራቱ በታዳጊ ሀገራት በተለይም እጅግ ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ ሀገራት፣በማደግ ላይ ያሉ ትንንሽ ደሴት መንግስታት እርስ በእርሳቸውና፣ የኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት እንዲሁም ባሉት ብሄራዊ፣አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ተቋማትን ወይም ድርጅቶች አማካኝነት ጭምር ፕሮቶኮሉን በአግባቡ ለመተግበር የአቅም ግንባታ፣የሰው ሀብትና የተቋማት አቅም የመገንባት ሥራዎችን በመተባበር ያከናውናሉ፡፡ በዚህ አገላለፅ አባል ሀገራት ወይም አባላት የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የግል ሴክተሮችን ጨምሮ ተሣትፎ እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ ፡፡

2. የታዳጊ ሀገራት በተለይም እጅግ ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ ሀገራት፣በማደግ ላይ ያሉ ትንንሽ ደሴት መንግስታት እርስ በእርሳቸውና፣ የኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት ይህንን ፕሮቶኮል ተግባራዊ ከማድረግ ጋር በተያያዘ ያላቸው የገንዘብ-ነክ ሀብት ፍላጐት በተገቢው የኮንቬንሽኑ ድንጋጌ መሰረት ለዚህ ፕሮቶኮል ተግባራዊነት አቅም የመገንባት ሂደት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡
3. ይህንን ፕሮቶኮል ተግባራዊ ከማድረግ ጋር በተያያዘ ለሚወሰዱ አግባብነት ያላቸው እርምጃዎች መሠረት ይሆን ዘንድ በማደግ ላይ ባሉ አባል ሀገራት በተለይም እጅግ ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ ሀገራት፣በማደግ ላይ ያሉ ትንንሽ ደሴት መንግስታት እርስ በእርሳቸውና፣ የኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት በሀገር ደረጃ በሚካሄድ ብሔራዊ የአቅም ምዘና የአቅም ግንባታ ፍላጐታቸውና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች መለየት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም እነዚህ ወገኖች በነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የአቅም ግንባታ ፍላጐትና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን በመለየት በሴቶች የአቅም ግንባታ

ፍላጎትና ቅድሚያ በሚሰጧቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

4. የዚህን ፕሮቶኮል ተግባራዊነት በመደገፍ ሂደት ውስጥ የአቅም ግንባታና ልማት ተግባራት የሚያተኩሩት ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ይሆናል፡፡

ሀ/ ይህንን ፕሮቶኮል ተግባራዊ የማድረግ እና የፕሮቶኮሉን ግዴታዎች የማክበርና የመፈፀም አቅም፡፡

ለ/ የጋራ ስምምነቶች ለማድረግ የመደራደር አቅም፣

ሐ/ አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት የሚመለከቱ የሀገር ውስጥ ሕጐች፣ አስተዳደራዊና የፖሊሲ እርምጃዎች የማዘጋጀት፣የመፈጸምና ተግባራዊ የማድረግ አቅም፣እና

መ/ ሀገራት ሀገር-በቀል የጥናትና ምርምር አቅም በማጐልበት የራሣቸው ጀነቲክ ሀብት ላይ እሴት ለመጨመር እንዲችሉ አቅም መፍጠር፣

5. ከዚህ በላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተገለፁት እርምጃዎች መካከል የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ/ የህግና የተቋማት ልማት፣

ለ/ በድርድር ሂደት ውስጥ ርትእ እና ፍትሐዊነት እንዲኖር ማበረታታት በጋራ ስምምነት ነጥቦች ላይ መደራደር የሚያስችሉ ስልጠናዎች መስጠት፣

ሐ/ በህጉ መሰረት መተግበሩን መከታተል፣

መ/ ለአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ሥራዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲከናወኑ ለማገዝ የተሻሉና ምርጥ የመገናኛ ዘዴዎችና ኢንተርኔት-ተኮር ሥርአቶችን መዘርጋት፣

ሠ/ የዋጋ ትመና ዘዴዎችን ማዘጋጀትና መጠቀም ፤

ረ/ የመድሃኒትነትና ሌሎች ጠቀሜታ ያላቸውን የእንስሳትና የእፅዋት ዝርያ መፈለግ፣ የአካላትን ምደባ ጥናት ማድረግ ና ተያያዥ ምርምሮችን ማካሄድ፣

ሰ/ ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር የመሠረተ ልማቶች እና የቴክኒክ አቅም ግንባታ ማካሄድ

ሸ/ የአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት ሥራዎች ለብዝሀ ህይወትና ክፍሎቹ ጥበቃና ዘለቄታዊ አጠቃቀም አስተዋጽኦ እንዲያደርግማስቻል

ቀ/ አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነትን በተመለከተ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አቅማቸው እንዲያሳድጉ ልዩ እርምጃዎችን መውሰድ፣ እና

በ/ የጀነቲክ ሀብት እና/ወይም ከጀነቲክ ሀብት ጋር የተያያዙ ባህላዊ እውቀቶች አርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት በተመለከተ የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦች በተለይም የሴቶችን አቅም ማጎልበት ላይ የተለዩ እርምጃዎችን መውሰድ፡፡

6. ከዚህ በላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 ድረስ በተዘረዘሩት መሠረት በብሄራዊ ፣ በአህጉራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የአቅም ግንባታ እና የእድገት ተኮር ሥራዎች ይበልጥ እንዲቀናጁ ለማድረግና ለማስተባበር እንዲቻል ለአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 23

## የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ትብብር እና ቅንጅት

በኮንቬንሽኑ አንቀፆች 15፣16፣18 እና 19 መሠረት አባል ሀገራት የባዮቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ጨምሮ በሚካሄዱ ቴክኒካዊ ሣይንሣዊ ጥናትና ምርምሮችና የልማት ፕሮግራሞች ውስጥ በጋራ በመተጋገዝና በመተባበር የፕሮቶኮሉን ግብ ለማሳካት ይጠቀሙበታል ፡፡

አባል ሀገራቱ በታዳጊ አባል ሀገራት በተለይም እጅግ ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ ሀገራት፣በማደግ ላይ ያሉ ትንንሽ ደሴት

መንግስታት እርስ በእርሳቸውና፣ የኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት ቴክኖሎጂዎችን እንዲያገኙና የቴክኖሎጂ ሽግግሮች እንዲኖር ተስማሚና ውጤታማ የቴክኖሎጂና ሣይንሳዊ መሠረቶችን በመጣል የኮንቬንሽኑና የዚህ ፕሮቶኮል ዓላማዎች ከግብ እንዲደርሱ በትብብር ይሰራሉ፡፡ የሚቻል ከሆነና አግባብነት ያለው ሆኖ ሲገኝ እነዚህ የትብብር ሥራዎች የጀነቲክ ሀብት ከሚያቀርብ ወይም ከሚያቀርቡ ወይም የጀነቲክ ሀብቱ መገኛ ከሆነ ወይም ከሆኑ ወይም በኮንቬንሽኑ መሠረት ጀነቲክ ሀብቱን ካገኘ ወይም ካገኙ አባል ሀገራት ጋር በመሆን በእነዚህ ሀገራት ውስጥ መካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 24

## አባል ያልሆኑ ሀገራት

የዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት አባል ያልሆኑትንሀገራት ፕሮቶኮሉን እንዲያከብሩና መረጃዎችን ለአርክቦትና የጥቅም ተጋሪነት አጣሪ ምክር ቤት በማቅረብ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ያበረታታሉ፡፡

## አንቀጽ 25

## ገንዘብ እና ሀብት ሀብትና የገንዘብ ማግኛ ዘዴ

1. ይህንን ፕሮቶኮል ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልግ የገንዘብ ሀብት በተመለከተ አባል ሀገራት በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 20 የተገለፀውን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባሉ፣

2. በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተገለጸውን የሀብትና የገንዘብ ማግኛ ዘዴ የዚህ ፕሮቶኮልም የገንዘብ ማግኛ ዘዴ ይሆናል፡፡
3. በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 22 ሥር የተመለከተውን የአቅም ግንባታና ልማትን በተመለከተ የፕሮቶኮሉ አባል ሀገራት ጉባኤ በመሆን የሚያገለግል የአባላት ስብሰባ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 የተመለከተውን የገንዘብ ሀብት ጉባኤው ሲወስን ታዳጊ አባል ሀገራትን በተለይም እጅግ ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ ሀገራት፣በማደግ ላይ ያሉ ትንንሽ ደሴት መንግስታት እርስ በእርሳቸውና፣ የኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት የነባርና የአካባቢ ማህበረሰቦችን እና በነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ ሴቶችን ጨምሮ የገንዘብ ሀብትና የአቅም ግንባታ ፍላጎት እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ፡፡
4. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 ሥር የተገለጸውን መሠረት በማድረግ አባል ሀገራት የታዳጊ አባል ሀገራትን በተለይም እጅግ ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ያሉ ሀገራት፣በማደግ ላይ ያሉ ትንንሽ ደሴት መንግስታት እርስ በእርሳቸውና፣ የኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ያሉ ሀገራት ፍላጐት ይህንን ፕሮቶኮል ተግባራዊ ለማድረግ የአቅም ግንባታና የልማት

ፍላጎታቸውን ለመለየትና ለመተግበር የሚያደርጉት ጥረት ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡

5. ይህንን ውል ከማጽደቅ ቀደም ብሎ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ጨምሮ ተያያዥ የአባል ሀገራት ጉባኤ ውሣኔዎች በተመለከተ በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተገለፀው የገንዘብ ማግኛ ዘዴ በዚህ አንቀጽ ውስጥ በተገለፁት ላይም ተፈፃሚነት ያለው ይሆናል፡፡
6. ያደጉ፣በማደግ ላይ ያሉ እና ኢኮኖሚያቸው በሽግግር ላይ ያሉ አባል ሀገራት የዚህን ፕሮቶኮል አንቀፆች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ገንዘብ፣ ሀብትና ሌሎች ግብአቶችን ለመጠቀም እንዲሁም ደግሞ ያደጉ ሀገራት ለማቅረብ በሁለትዮሽ፣በክልላዊና በባለ ብዙ ወገን የአሰራር መስመሮች በኩል አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 26

## የዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ጉባኤ የአባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ ስለማገልገል

1. የአባል ሀገራቱ ጉባኤ የዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. የዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ያልሆኑ የኮንቬንሽን አባል ሀገራት በማንኛውም ለዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት እንደ

ስብሰባ በሚያገለግሉ ጉባኤዎች ላይ በታዛቢነት ለመሳተፍ ይችላሉ፡፡ ጉባኤዎች እንደ ፕሮቶኮሉ አባል ሀገራት ስብሰባ በሚያገለግሉበት ጊዜ በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት ውሳኔ የሚወሰነው በፕሮቶኮል አባል ሀገራት ብቻ ይሆናል፡፡

3. የአባል ሀገራት ጉባኤ የዚህ ፕሮቶኮል የአባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ በሚያገለግልበት ወቅት ማንኛውም የኮንቬንሽኑን አባል ሀገር በመወከል የአባል ሀገራት ጉባኤ ቢሮ አባል የሆነና ነገርግን በወቅቱ የዚህ ፕሮቶኮል አባል ያልሆነ አካል የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ከሆኑት መካከል በአባል ሀገራቱ በሚመረጠው አካል የሚተካ ይሆናል፡፡

4. የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ጉባኤ ሆኖ የሚያገለግል የአባል ሀገራት ስብሰባ የዚህን ኘሮቶኮል ትግበራን በተመለከተ በየጊዜው መደበኛ ግምገማ ያካሂዳል እንዲሁም በተሰጠው ሥልጣን ገደብ ውስጥ አፈጻጸሙን ውጤታማ ለማድረግና ለማገዝ አስፈላጊውን ውሳኔ ይወስናል ፡፡ በተጨማሪም በዚህ ኘሮቶኮል መሠረት የተሰጡት ሌሎች ተግባራትና ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ያከናውናል፡፡

   ሀ. ይህንን ኘሮቶኮል ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ በሆኑ ማንኛውም ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ አስተያየቶችን ይሰጣል፣

ለ. ይህንን ኘሮቶኮል ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ንዑስ አካላት ያቋቁማል፣

ሐ. ብቃት ካላቸው አለምአቀፍ ድርጅቶች ፣ በመንግስታት መካከል እና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚቀርቡ የድጋፍ፣ የአገልግሎቶችና የትብብር እና የመረጃ አገልግሎቶች አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ ያፈላልጋል ይጠቀማል፣

መ. በዚህ ኘሮቶኮል አንቀጽ 29 መሠረት የሚቀርቡ መረጃዎችን ለማስተላለፍ የሚቀርቡበትን አቀራረብ ያዘጋጃል ጊዜን ይወስናል እንዲሁም በማንኛውም ንዑስ አካላት የሚርቡለትን መረጃዎችን እና ሪፖርቶች ይመለከታል፣

ሠ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህን ፕሮቶኮል እና አባሪዎቹን እንዲሁም የተጨማሪ አባሪዎችን ማሻሻያ ለፕሮቶኮሉ ተግባራዊነት አስፈላጊ መሆናቸው ሲታመንበት ይመረምራል፣ ያፀድቃል እና

ረ. ለዚህ ኘሮቶኮል ተግባራዊነት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

5. ለዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት እንደ ስብሰባ በሚያገለግሉ ጉባኤዎች በስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር

የአባል ሀገራት ጉባኤ ደንቦችና ስነስርአቶች እንዲሁም የኮንቬንሽኑ የፋይናንስ ደንቦች በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ኘሮቶኮል ውስጥ በተገለጹት ጉዳዮች ላይም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

6. የዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት እንደ ስብሰባ በሚያገለግል የአባል አገራት ጉባኤ የመጀመሪያው ስብሰባ በፅህፈት ቤቱ የሚጠራ ሆኖ ይህ ፕሮቶኮል ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን በኋላ ከሚጠራው የአባል ሀገራት ጉባኤ የመጀመሪያ ስብሰባ ጋር አንድላይ የሚካሄድ ይሆናል፡፡በዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ የሚያገለግል የአባል ሀገራት ጉባኤ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር በፕሮቶኮሉ  የአባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ የሚያገለግል የአባል ሀገራት ጉባኤ ከመደበኛ የአባል አገራት ጉባኤ ጋር የሚደረጉ ይሆናል፡፡
7. የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ የሆነ የአባል ሃገራት ጉባኤ የተለየ ስብሰባ በዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ በሆነ የአባል ሀገራት ጉባኤ ውሣኔ መሠረት አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ጊዜ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ወይም ማንኛውም አባል በጽሑፍ ለፅህፈት ቤቱ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ጥያቄ ካቀረበና ሌሎች አባል ሀገራት በፅህፈት ቤቱ በኩል

እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ ጥያቄው ቢያንስ አንድ ሦስተኛ የአባል ሀገራት ድጋፍ ካገኘ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

8. የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ጉባኤ የሆነ የአባል ሀገራት ስብሰባ ላይ የተባበሩት መንግሥታት የተለዩ ኤጀንሲዎች እና አለምአቀፍ የአቶሚክ ኃይል ድርጅት እንዲሁም ማንኛዉም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ሀገራት ወይም የኮንቬንሽኑ አባል ያልሆኑ ሀገራት በታዛቢነት ለመሣተፍ ይችላሉ፡፡ ብሄራዊም ሆነ አለምአቀፋዊ ወይም መንግስታዊ የሆነ ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ማንኛውም አካል ወይም ወኪል በዚህ ኘሮቶኮል መሠረት መስፈርቶችን የሚያሟላ አካል በጉባኤው ላይ ለመገኘት ፍላጎት ያለው መሆኑን ለፅህፈት ቤቱ ካስታወቀና የዚህ ኘሮቶኮል አባል አገራት ጉባኤ የሆነ የአባል ሀገራት ኮንፈረንስ ከአባል አገራቱ ቢያንስ በአንድ ሦስተኛ ተቃውሞ ካልገጠመው በስተቀር በታዛቢነት ሊሣተፍ ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ ካልተገለፀ በስተቀር በስብሰባ ላይ በታዛቢነት ለመሣተፍ ፈቃድም ሆነ ተሳትፎ የሚሰጠው በዚህ አንቀጽ ውስጥ በተራ ቁጥር 5 ሥር በተገለጸው ስነስርዓት መሠረት ሲወሰን ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 27

# ንዑሣን አካላት

1. የአባል ሀገራት ጉባኤ እንደ ስብሰባ የሚያገለግሉ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ውሳኔዎችን ጨምሮ በኮንቬንሽኑ ሥር የተቋቋሙ ንዑሣን አካላት በዚህ ፕሮቶኮል ውስጥም ሊያገለግል ይችላል። የዚህ ዓይነቱ ውሣኔ የሚከናወኑ ተግባራትን ለይቶ ማስቀመጥ ይኖርበታል ።
2. የዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ያልሆኑ የኮንቬንሽኑ አባል ሀገራት የንዑሣን አካላት በማንኛውም ስብሰባ ላይ በታዛቢነት ለመሣተፍ ይችላሉ። የኮንቬንሽኑ ንዑሣን አካላት የዚህ ፕሮቶኮል ንዑሣን አካላት ሆነው ሲያገለግሉ ይህንን ፕሮቶኮል የሚመለከቱ ውሣኔዎች በፕሮቶኮሉ አባል ሀገራት ብቻ እንደተደረጉ ይቆጠራል።
3. አንድ የኮንቬንሽኑ ንዑስ አካል ይህንን ፕሮቶኮል የሚመለከቱ ተግባራቶቹን ሲያከናውን ማንኛውም የኮንቬንሽኑን አባል ሀገር የሚወክል የንዑስ አካሉ ቢሮ አባል በወቅቱ የዚህ ፕሮቶኮል አባል ያልሆነ እንደሆነ ከዚህ ፕሮቶኮል አባል ሀገራት መካከል በአባል ሀገራቱ በሚመረጥ አባል የሚተካ ይሆናል።

## አንቀጽ 28

## ፅህፈት ቤት

1. በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 24 መሠረት የተቋቋመው ፅህፈት ቤት የዚህ ኘሮቶኮል ፅህፈት ቤት ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል፡፡
2. በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 24 ተራ ቁጥር 1 ሥር የተዘረዘሩት የፅህፈት ቤቱ ተግባራት ይህንን ኘሮቶኮል በተመለከተም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡
3. ተለይተው የሚታወቁ እስከሆኑ ድረስ ለዚህ ኘሮቶኮል የፅህፈት ቤቱ ወጪዎች በኘሮቶኮሉ አባል ሀገራት የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡ ይህንን በተመለከተ የሚያስፈልገውን በጀት በዚህ ኘሮቶኮል የአባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ በሚያገለግል የአባል ሀገራት ጉባኤ የመጀመሪያ ስብሰባ ላይ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 29

## ክትትል ማድረግና ሪፖርት ማቅረብ

እያንዳንዱ አባል ሀገር በዚህ ኘሮቶኮል መሠረት ያሉበትን ግዴታዎች ተግባራዊነት በተመለከተ ክትትል ያደርጋል፣ በየወቅቱም የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ በሚያገለግል የአባል ሀገራት ጉባኤ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረት ይህንን ኘሮቶኮል ተግባራዊ ለማድረግ የወሰዳቸውን እርምጃዎች

በተመለከተ የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ በሚያገለግል የአባል ሀገራት ጉባኤ ላይ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 30

## የዚህን ኘሮቶኮል ተፈፃሚነት ለማጠናከር የሚረዱ ስነ-ስርዓቶችና ዘዴዎች

የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ በሚያገለግል የአባል ሀገራት ጉባኤ በመጀመሪያ ስብሰባው የዚህን ኘሮቶኮል አንቀፆች ተግባራዊ የማድረግ ሂደትን የሚያጠናክሩ የትብብር ስነስርአቶችን ፣ ተቋማዊ አሰራሮችን ይመረምራል ያፀድቃል እንዲሁም የማይተገበሩ ጉዳዮችን መፍትሄ ይሰጣል እንደአስፈላጊነቱ እነዚህ ስነስርዓቶችና አሰራሮች ምክርና እርዳታ መስጠትን የሚመለከቱ አንቀፆችን ያካትታሉ፡፡ እነዚህ በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 27 ውስጥ የተገለፁት እንደተጠበቀ ሆነው የአለመግባባት አፈታት መመሪያዎችና አሠራሮች ተለይተው የሚታዩ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 31

## ምዘናና ክለሳ

የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ በሚያገለግል የአባል ሀገራት ጉባኤ ይህ ኘሮቶኮል ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ከአራት

አመታት በኃላ ሲሆን ከዚያ በኋላ ያሉትን በተመለከተ የዚህ ኘሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ሆኖ በሚያገለግል የአባል ሀገራት ጉባኤ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ የዚህን ኘሮቶኮል ውጤታማነት በተመለከተ ግምገማ ያካሂዳል፡፡

## አንቀጽ 32

## ፊርማ

ይህ ኘሮቶኮል በኮንቬንሽኑ አባል ሀገራት ከየካቲት 2/2011 እስከ የካቲት 1/2012(እ.ኤ.አ) ድረስ በተባበሩት መንግሥታት ዋና መ/ቤት በኒውዮርክ ለፊርማ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡

## አንቀጽ 33

## ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

1. ይህ ኘሮቶኮል የኮንቬንሽኑ አባል የሆኑ ሀገራት ወይም ክልላዊ የኢኮኖሚ ትብብር ድርጅቶች ሃምሣኛ የማጽደቂያ፣የመቀበል፣ የድጋፍ ወይም የስምምነት ዶኩሜንት ካስቀመጡበት ከዘጠናኛ(90) ቀን በኃላ ተፈጻሚነት ያገኛል፡፡
2. ይህ ፕሮቶኮል ተፈፃሚ መሆን የሚጀምረው አንድ ሀገር ወይም ክልላዊ የኢኮኖሚ ትብብር ድርጅት ይህን ፕሮቶኮል ያፀደቁት፣የተቀበሉት፣የደገፉት ወይም የተስማሙት ወይም ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 ስር በተገለፀው መሠረት ሀምሳኛ

የስምምነት ዶኩሜንት በማስቀመጥ ፣አንድ ሀገር ወይም ክልላዊ የኢኮኖሚ ትብብር ድርጅት የማፅደቂያ፣የመቀበያ፣የድጋፍ ወይም የመስማሚያ ዶኩሜንት ካስቀመጡበት ከዘጠናኛው ቀን ጀምሮ ወይም ለሀገራት ወይም ክልላዊ የኢኮኖሚ ትብብር ድርጅት ኮንቬንሽን ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

3. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ሥር ለተገለፁት አገልግሎቶች በክልላዊ የኢኮኖሚ ትብብር ድርጅት የተቀመጠ ማንኛውም ዶኩሜንት የድርጅቱ አባል ሀገራት ባስቀመጡት ላይ እንደ ተጨማሪነት ተወስዶ አይቆጠርም፡፡

## አንቀጽ 34

## የተፈጻሚነት ገደብ

ይህንን ኘሮቶኮል በተመለከተ የተፈጻሚነት ገደብ አይኖርም፡፡

## አንቀጽ 35

## ከአባልነት ስለመውጣት

1. ይህ ኘሮቶኮል ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ከሁለት አመታት በኃላ በማንኛውም ጊዜ ኘሮቶኮሉን ፈርሞ የነበረ አባል በጽሑፍ በማሣወቅ ከአባልነት ለመውጣት ይችላል፡፡

2. ማናኛውም የዚህ ዓይነት ከአባልነት የመውጣት ሂደት ተፈጻሚ የሚሆነው ማሳሰቢያው ለኮንቬንሽኑ ፅህፈት ቤት ከደረሰበት ወይም በማመልከቻው ላይ በግልፅ ከተቀመጠው ቀን ጀምሮ ከአንድ አመት ጊዜ በኋላ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 36

## የተረጋገጡ ፅሁፎች

የዚህ ኘሮቶኮል ኦሪጅናል ሠነድ በአረብኛ፣ በቻይንኛ፣ በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሣይኛ፣ በሩሲያኛ እና በስፓንኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ፅህፈት ቤት ይቀመጣል፡፡

ከላይ የተገለጹትን በሙሉ በመቀበል ከዚህ በታች ፊርማቸውን ያኖሩት አካላት በተጠቀሰው ቀን ኘሮቶኮሉን ፈርመዋል፡፡

በዛሬው እለት ጥቅምት 29/2010 እ.ኤ.አ በናጐያ ከተማ ተፈረመ፡፡

## አባሪ

**ገንዘብ ነክ እና ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ጥቅማጥቅሞች፡-**

1. ገንዘብ ነክ ጥቅሞች በነዚህ ብቻ ባይወሰንም የሚከተሉትን ያካትታል

ሀ. የአርክቦት ክፍያዎች በተሰበሰበው ናሙና ወይም በተገኘው መጠን ልክ የሚከፈል ይሆናል፣

ለ. የቅድሚያ ክፍያዎች፣

ሐ. በየደረጃው የሚፈጸሙ ክፍያዎች፣

መ. የሮያሊቲ ክፍያዎቸ፣

ሠ. ለንግድ አላማ ሲሆን የፍቃድ ክፍያዎች፣

ረ. ዘላቂነት ያለው የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ እና ተጠቃሚነትን ለሚደግፉ የሚከፈል ልዩ ክፍያዎች፣

ሰ. በጋራ ስምምነት መሠረት የሚከፈሉ የደመወዝ ክፍያዎች፣

ሸ. ለምርምር የሚውል የገንዘብ ክፍያ፣

ቀ. የጣምራ ሥራዎች እና

በ. ለተገቢው ተያያዥ የአእምሮ ንብረት መብት የጣምራ ባለቤትነት ክፍያዎች

2. ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ጥቅሞች በነዚህ ብቻ ባይወሰንም የሚከተሉትን ያካትታል

ሀ. የጥናት፣ምርምርና ልማት ውጤቶችን ማጋራት፣

ለ. በሣይንስ ጥናትና ምርምር መርሃ ግብሮች እና በልማት ውጤቶች በተለይም በባዮቴክኖሎጂ የምርምር ተግባራት ውስጥ ከተቻለ ጀነቲክ ሀብት አቅራቢ በሆነ ሀገር ውስጥ በሚካሄዱት ተግባራት በጋራ በመተባበር፣በመተጋገዝና አስተዋፅኦ በማድረግ ፣

ሐ. የልማት ምርት ውስጥ መሣተፍ፣

መ. በትምህርትና ሥልጠና ላይ መተባበር ፣መቀናጀት እና አስተዋጽኦ ማድረግ

ሠ. የኢ-ዘቦታ ጀነቲክ ሀብት ተቋም እና የመረጃ ቋት ቅበላ፣

ረ. የጀነቲክ ሀብት አቅራቢ ለሆነው ወገን እጅግ ፍትሐዊና ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የቴክኖሎጂ እና እውቀት ሽግግር እንዲኖር ማድረግ በተለይ ም በምርጫ እና በስምምነት ሕይወታዊ ብዝሀነትን ለመንከባከብና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችሉ ባዮቴክኖሎጂን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው ሌሎች እውቀቶችና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ማቅረብ፣

ሰ. የቴክኖሎጂ ሽግግር አቅም ማጐልበት፣

ሸ. ተቋማዊ አቅም መገንባት፣

ቀ.የአርክቦት መመሪያዎችና ደንቦችን ተፈጻሚ ለማድረግና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አቅም ለመፍጠር የሰው እና የቁሳቁስ ሀብት ማቅረብ፣

በ. ከጀነቲክ ሀብት ጋር ተያያዥ የሆኑ ስልጠናዎችን ጀነቲክ ሀብት አቅራቢ የሆኑ ሀገራት ሙሉ ተሣትፎ ባለበትና በተቻለ በእነዚህ ሀገራት ውስጥ መስጠት፣

ተ. ብዝሀ ህይወትን ለመጠበቅእና ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመጠቀም የእንስሳትና የእፅዋት ምደባ ጥናት፣ስነ

ህይወታዊ ቆጠራዎችን፣ጥናቶችን እና ሳይንሳዊ መረጃዎችን ማቅረብ፣

ቸ. በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ አስተዋጽኦ ማድረግ፣

ነ. የጀነቲክ ሀብት አቅራቢ የሆነውን ወገን የጀነቲክ ሀብት አጠቃቀም ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እንደ ጤና እና የምግብ ዋስትና ባሉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ጥናትና ምርምር፣

ኘ. ከአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ስምምነትና ከዚህ ጋር በተያያዘ በቀጣይነት በጋራ ከሚከናወኑ ተግባራት የሚመነጩ ተቋማዊና ሙያዊ ግንኙነቶች፣

አ. የምግብና የኑሮ ዋስትና ጥቅሞች፣

ከ.ማኅበራዊ እውቅና

ወ. አግባብነት ያላቸው የአእምሯዊ ሀብት መብቶች የጋራ ባለቤትነት።